# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

መጋቢት 7 ቀን፥ 09)(8 ዓ.ም.

ይድረስ፦
ለጋአ ዘወልደ ቂርቆስ፡፡

ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ስም አቀርባለሁ፡፡

በእ-ደብዳቤ (እለቁጥሩ ደብዳቤ = electronic mail = email) ልከውልኝ፡ አጭር መልስ ከሰጠሁበት ደብዳቤዎ በኋላ፡ በሰፊው የጻፉልኝ፡ ኹለተኛውም ደረሰኝ፤ ለኹሉም፡ እንደገና እግዜር ይስጥልኝ! ኹለቱንም ደብዳቤዎችዎን፡ በጥሞና ተመልክቻቸዋለሁ፡፡

ያነበቧቸውን የመጻሕፍቴን መልእክቶችና በቅርቡ የተላለፈውን የጾመ ኢትዮጵያን ጥሪ መሠረት በማድረግ፡ በእነዚሁ ደብዳቤዎችዎ ውስጥ፡ ለሠነዘርዋቸው መልካካም አስተያየቶችዎ፡ አድናቆቴንና ሙገሳዬን አስቀድማለሁ፤ ታላላቅ ቁም ነገሮችን ይዘው ለቀረቡት፡ ብርቱ ጥያቄዎችዎም፡ አጠቃላይ የሚኾነውን የመፍትሔ መልሴን፡ እንደሚከተለው፡ ባጭር ባጭሩ አስከትላለሁ፦

1ኛ፡ ከደብዳቤዎ፡ በአንዱ ላይ እንዳወሱት፡ ከኹለት ዓመታት በፊት፡ እርስዎ፡ በዚሁ፡ በኀዋው መስመር፡ ባስተላለፉልኝ መልእክትዎ መነሻነት፡ ከተገናኘን በኋላ፡ ያ ግንኙነት፡ በእኔ መልስ አብቅቶ፡ የተቋረጠ ሲኾን፡ አኹን፡ ይኸው ግንኙነታችን፡ እንደገና እንዲቀጥል፡ የኢትዮጵያ አምላክ ፈቃዱ ስለኾነ፥ ይልቁንም፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ እርሱን በእውነት በሚፈልጉት ልቦና ውስጥ አድሮ፡ የእርሱን እውነት በሚያሳውቀውና በሚያናግረው፥ በሚያስሠራውና በሚያስፈጽመው፡ በቅዱስ መንፈሱ አሳስቦዎ፡ በእነዚህ ደብዳቤዎችዎ ውስጥ የገለጿቸውን ፍሬ አሳቦች ኹሉ ስላስጻፈዎ፡ አመስግኜዋለሁ፡፡

ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ስለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ሲሉ፡ ገድላቸውን ፈጽመው፡ በሰማዕትነት ያረፉትን፡ የወላጅ አባትዎን ፈለግ ተከትለው፥ የዚህኑ፡ የቅዱሱን ኪዳን ባለአደራነት ጋሻ አንሥተውና ተረክበው፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ግዳጅዎን በማካኼድ ይቀጥሉ ዘንድ፡ እርስዎን የመሰሉትን ታማኞች ወገኖቹን፡ እንዲህ እያስነሣና እየመለመለ፡ ገና በአካለ ሥጋም ባይኾን፡ በአካለ መንፈሱ እንድንገናኝና እንድንሰባሰብ ማድረጉን፡ እነሆ እመለከታለሁ፤ ይህ መኾኑ፡ በዚህ ረገድ ያስጀመረን አገልግሎት እየተጠናከረና እየሰፋ በመኼድ ላይ መኾኑን ማሳወቁ ነውና፡ ፈቃዱ ኾኖ፡ በአካለ ሥጋ እስኪያገናኘን ድረስ፡ በያለንበት እንድንበረታ፡ እኔም በበኩሌ፡ አደራ እላለሁ፡፡


መልእ. ሣ. ቁ. 8)02፣ ስልክ ቁ. 06-08-*5፣ "--*5፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

በአባትዎ ላይ አድሮ፡ ያን ገድል ያሳሰበ፥ ያናገረና እስከሞት ድረስ አስጨክኖ ያስፈጸመ፥ ዛሬ ደግሞ፡ በልጆቸው፡ በእርስዎና እርስዎን በመሰሉትም ላይ አድሮ፡ ያንኑ ዓይነት ገድል አሳስቦና አስጨክኖ ለማስፈጸም፡ የሚያናግረውና የሚያስጽፈው፡ ያው፡ አንዱ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ መኾኑ፡ በዚህ ግንኙነታችንና ኹላችን፡ ከእርሱ ተቀብለን በምንጋደልለት በመልእክታችን ተመሳሳይነትና አንድነት መረጋገጡ፡ ይኸው ይታያል።

2ኛ፡ ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ያን፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጥንታዊ አቋሙን መልሶ መያዙን ሲያረጋግጥ፡ በኢትዮጵያም ኾነ፡ በውጪው ዓለም የሚኖረው እምነተ ቢሱና አረማዊው አሕዛብ፥ ይሁዲውና እስላሙ፥ ክርስቲያኑም ሳይቀር፡ ኹሉም፡ ደስ ብሎት፡ እንደጥንቱ፡ በፍቅርና በሰላም የሚቀበለው እንጂ፡ እንኳንስ ሁከትንና ጦርነትን ሊያነሣበት ይቅርና፡ ሥውር ተቃውሞንና ቅሬታን እንኳ ሊያሳየው፡ ከቶ አይቃጣም፤ ምክንያቱም፡ እኒህ ወገኖች፡ እያንዳንዳቸው፡ ከጥንት ጀምረው፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ እውቅናን ሰጥተው፡ ኢትዮጵያን፡ በኢትዮጵያነቷ፥ ኢትዮጵያውያንንም፡ በኢትዮጵያዊነታቸው የተቀበሏቸው፥ ያከበሩዋቸውና በተለይም፡ በየራሳቸው አገር፡ የሃይማኖት መከራና ስደት በደረሰባቸው ጊዜያት ኹሉ፡ እያንዳንዳቸው፡ ወደእነርሱ ሸሽተው በመምጣት፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ የተማጠኗቸው፡ በዚህ፡ እኛ ዛሬ በምንጋደልለት በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንና ሥርዓተ መንግሥታችን ጸንተው በመገኘታቸው መኾኑን፡ ኹላቸው፡ በየሃይማኖታቸው ስለሚያውቁትና ይህንኑ እውነታ፡ አጽድቀው ስለተቀበሉት መኾኑ፡ ማንም ሊያስተባብለው የማይቻለው ግዙፍ የምስክር ሓውልት ኾኖ የኖረ ሓቅ ነው።

በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለውን፡ ይህን ኹሉ ችግርና ምስቅልቅል የፈጠርነው እኮ፡ እነርሱ፡ ባዕዳኑ ሳይኾኑ፡ እኛው ራሳችን ኢትዮጵያውያኑ ነን! ይኸውም፡ በእነዚሁ፡ በሌሎቹ ሃይማኖታውያን ዘንድ የታወቅንበትንና የተወደድንበትን፥ የተከበርንበትና የተፈራንበትን፡ ብርቅ ሞገሳችንን፥ መከላከያ ጋሻችንንና መከበሪያ ዘውዳችንን፡ <u>እግዚአብሔርንና ቅዱሱን ኪዳኑን፡</u> እኛው ራሳችን፡ ንቀንና ወርውረን ስለጣልነው እኮ ነው! በዚህ ጊዜና ለዚህ እኮ ነው፡ በእነርሱ በኩል፡ “እናንተና እኛ፡ ተዋውቀንና ተከባብረን የኖርንበትን፡ ይህን፡ ከእግዚአብሔር፡ በአደራ ተቀብላችሁ፥ አባቶቻችሁና እናቶቻችሁም ጠብቀው ያቆዩዋችሁን መለኮታዊ ቅርሳችሁን፡ እናንተ ራሳችሁ፡ አሽቀንጥራችሁ ጥላችሁ ከተዋችሁት፡ ኢትዮጵያን ለመያዝ ለሚያስችለውና ለሚያበቃው፡ ለተከታዩ ባለመብትነትማ፡ እኛ እንቀርባለን!” በማለት፡ ኹሉም የሃይማኖት ወገኖች፡ የቅደም ተከተል ተራቸውን ይዘው መኮልኮል፡ አግባብና አስፈላጊ የኾነባቸው፡፡ በሙታን አርባ ቀን፡ የቤተሰብ ተወላጆች፡ ለውርስ ኑዛዜ፡ የዘር ሓረጋቸውን ተራ ቆጥረውና ተሰልፈው እንደሚቀርቡ፡ ማለት ነው።

ስለዚህ፡ አኹን ላለው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የቀረበለት፥ አማራጭ የሌለውና ብቸኛ የኾነው መልካም ዕድል፡ እናት አገሩን ኢትዮጵያን፥ የቀደሙ አባቶቹንና እናቶቹን፡ ኢትዮጵያውያንም፡ ለዝንተ ዓለም፡ በነጻነትና በክብር ወዳኖረው፡ ወደዚህ፡ እኛ፡ ዛሬ፡ ጸንተን ወደቀጠልንበት፡ ወደጥንታዊው፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱና ሥርዓተ መንግሥቱ፡ በእውነተኛ ንስሓ መመለስ ብቻ ነው።

3ኛ፡ ይህን ቁርጥ ዓላማ፡ በሥራ ላይ ዐውሎ፡ እውን ለማድረግ ደግሞ፡ በቅድሚያ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ እየራሱን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ በእውቀትና በንስሓ ማብቃት ይኖርበታል፤ በዚህ ጊዜ፡ የሚያስበው፥ የሚናገረውና የሚያደርገው ኹሉ፡ የእውነት፥ በእውነትና ለእውነት ይኾናል፤ ባጭሩ፡ ይህ ኢትዮጵያዊ፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ኾኖ፡ በምድር ላይ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የምታስገኘውን ሕይወት፡ በሥጋ ጭምር፡ መኖር የቻለ ባለዕድልና ባለድል ይኾናል፤ “ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት”፡ የሚለው ሕልውናና ዘይቤ፡ በዚህ ኢትዮጵያዊ ሕያው ሰውነት ላይ ፍጹም እውንና የገዘፈ ገሃድ ኾኖ ይገለጻል።

በዚህ ጊዜ፡ “እውነት እውነት እላችኋለሁ! በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤” የሚለው የመሪያችን አምላካዊ ቃል፡ በዚያ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ላይ ተፈጻሚ ለመኾን ይበቃል። ይህ ኢትዮጵያዊ፡ እርሱን የመሰለ አንድ ባልንጀራን ካገኘ፥ “ከእናንተ፡ ኹለቱ፡ በምድር፡ በማናቸውም፡ በሚለምኑት ነገር ኹሉ ቢስማሙ፡ በሰማያት ካለው፡ ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል!” ያለው፥ ወይም፡ እነዚህ ኹለቱ፡ ሌላ ሦስተኛ ባልንጀራን ከጨመሩ ደግሞ፡ “ኹለት፥ ወይም ሦስት፡ በስሜ በሚሰበሰቡበት፡ በዚያ፡ በመካከላቸው እኾናለሁ!” ያለው ቃሉ፡ በእነርሱ ላይ ተፈጻሚ ይኾንና፡ ለኹሉ የሚበጀውን፥ የሚያጠግበውንም፡ ጣፋጩን የሕይወት ፍሬ፡ ለአገራቸውና ለወገናቸው፡ ማበርከት ይጀምራሉ።

የእነዚህ ዓይነቶቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ቍጥር፡ ጥቂት በርከት ሲል፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፡ መልካም ሕይወት ይኾንላቸው ዘንድ፡ ከሥነ ፍጥረቱ ጋር ሠርቶ የሰጣቸውን፡ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነትን ጸጋና በረከት፥ ክብርና ማዕርግ፡ ወደግለሰቦች ብቻ ሳይኾን፡ ቀድሞ ወደነበረበት፡ ወደቤተሰብነት፥ ከዚያ፡ ወደኅብረተሰብነት፥ አያይዞም፡ ወደሕዝባዊነትና ብሔራዊነት የመመለሱ፥ በመጨረሻም፡ ወደአጥቃላዩ ዓለም አቀፍነት የማብቃቱ ተግባር፡ ምቹ፥ ቀናና ቀላል ይኾናል።

ከዚህ በኋላ፡ ሥነ ፍጥረት ሳትቀር፡ በምድረ ኢትዮጵያ፡ ቀናንሳውና ነሣሥታው የነበረውን መድበል ጸጋዋን፡ እንደገና አለምልማና አትረፍርፋ፥ የክፉው ጠንቅ የኾኑትን ችጋርንና ደዌያትን አስወግዳ፡ መለኮታዊ ልግሥናዋን መልሳ የምታበረክታቸው ትኾናለች፤ እኒህ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ ለወገኖቻቸው ኹሉ፡ ለነፍሳቸውና ለሥጋቸው፥ ለመንፈሳቸውም የሚያስፈልጓቸውን፡ የልማትና የዕድገት ምግባራት፡ በፍቅርና በሰላም፥ ነጻ በኾነውም፡ የታማኝነት አገልግሎታቸው፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በአገር ደረጃ ለማከናወን የሚችሉበትን አምላካዊ ጥበብ፥ ሀብትና ኃይል ይቀዳጃሉ፤ በጎ የኾነውን ነገር ኹሉ ለማድረግ ይቻላቸዋል፤ የሚሳናቸው፡ አንዳችም ነገር አይኖርም። (ማቴ. 08፥ 09-"፤ ዮሐ. 04፥ 02።)

የእነዚህን፡ ከላይ የተጠቀሱትን እውነታዎች ዝርዝር ሓተታ፡ ምናልባት፡ ገና ካላነበቧቸው መጻሕፍቴ የቀረ ነገር ቢኖር፡ ያን፡ ወደፊት እንደሚደርሱበት በማመን፡ እስካኹን ከተመለከቷቸው ጽሑፎቼና መጻሕፍቶቼ፥ በቅርቡም፡ (እርስዎ፡ ካዩት በኋላ፡ የወጣውን፡ ዋናውንና ትክክለኛውን ቅጂ፡ እንደገና እንዲመለሱበት እየጋበዝሁዎ፡) ለመዲናው የእስልምና አማኝ ጠያቂ፡ ከሰጠሁት መልስ እንደተገነዘቡት አምናለሁ።

4ኛ፡ የዚህን አገልግሎታችንን ዓላማ በበለጠ ወደሕዝቡ አስፋፍቶ ለማዳረስ፡ አኹን ያለው፡ የመጻሕፍትና የዕትሞች ሥርጭት፥ የጎዋ ሰሌዳ (website) እና የእ-ደብዳቤ ማስተላለፊያ ብቻ ሳይበቃ፡ የጦማረ ሕዝብ (gazetta) እና የመጽሔት ዝግጅት መጀመርና ማሠራጨት ተግባርን ማካኼድ፡ እጅግ አስፈላጊና ተገቢ ስለመኾኑ፡ ያቀረቡት አሳብ፡ ድንቅ ነው፤ እኛም በሥራ ላይ ልናውለው፡ አመቺውን ጊዜ እየጠበቅን፡ የቆየንበት ዕቅድ ስለኾነ፡ ፈቃደ እግዚአብሔር ኾኖ፡ እኔ፡ በቅርቡ፡ ወደኢትዮጵያ በምመለስበት ጊዜ፡ ውጥኑ ስለሚፈጸምበት ይዞታ፡ ቃል ለቃል ተነጋግረንበት የምንጨርሰው ጉዳይ ይኾናል፤ እስከዚያውም፡ እዚያው አዲስ አበባ ካሉት አገልጋዮች ጋር ስትመካከሩበት ብትቆዩ ይጠቅማል።

5ኛ፡ ከመግቢያው ላይ እንደጠቀስሁት፡ የዛሬ ኹለት ዓመት ግድም፡ በእርስዎ የእ-ደብዳቤ የተጀመረው የጎዋ መጻጻፍ ግንኙነታችን፡ ለምን እንደተቋረጠ፡ ምክንያቱን፡ እኔ ባላውቀውም፡ እርስዎ ያውቁታል። በዚህ አገልግሎታችን አንጻር፡ ያለው ተቃዋሚው ኃይል ማን፥ ምን እንደኾነ፡ ያለማቋረጥ፡ በእውነተኞቹ ሓዋርያት አንደበት እየተነገረ እንደሚሰማ፥ በቅዱሳት መጻሕፍትም ተጽፎ እንደሚነበብ ኹሉ፡ መንፈስ ቅዱስም፡ ምንጊዜም፡ ለማንኛዎቹም ታማኞች አገልጋዮቹ፡ አስቀድሞ ስለሚገልጸው፡ ኹላችንም እንደምናውቀው አልጠራጠርም።

*እርስዎም፡ ይህንኑ፡ በአንደኛው ደብዳቤዎ ውስጥ፡ “የእርስዎን መጻሕፍት ካነበብሁ በኋላ፡ (ማለትም፡ 'ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!' እና 'ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት') ምን ያህል የተደበቁ ምሥጢራት ያሏት ታላቅ ሀገር እንዳለችን፡ መረዳት ብቻ ሳይኾን፡ ይኼን ምሥጢርዋን ደግሞ፡ አንዳንዶች፡ ባለማወቅ፥ ሌሎች፡ በምቀኝነትና በቅናት፥ ሌሎች ደግሞ፡ በንዝኅላልነትና ባለማስተዋል፡ ሊያዳፍኑትና ሊያጠፉት እንደሚውቸረቸሩ፡ ማስተዋል ችያለሁ።”* ሲሉ ገልጸውታል።

*አዎን!* *ተቃዋሚዎቻችንን፡ ሥጋውያኑንም ኾነ መንፈሳውያኑን፥ የራሳችንንም ኾነ* ባዕዳኑን፡ ደህና አድርገን እናውቃቸዋለን። በመናፍስቱ ዓለም፡ ዲያብሎስ ከሚመራው፡ ከርኩሳን አጋንንት ሠራዊት ጀምሮ፡ ግዙፉን ዓለም፡ አጠቃልለው ለመግዛት እስከሚራወጡት፡ እስከኃያላኑ ሰብኣውያን መንግሥታት ድረስ ያሉትን ማለት ነው፤ እነዚህ ኹሉ፡ እነርሱ፡ በገለልተኝነት ቁጭ ብለው፡ እኛኑ ራሳችንን መሣሪያ አድርገው በመጠቀም፡ እርስ በርሳችን ለያይተውና ራሳችንን፡ በራሳችን አጨራርሰው ሲፈጁን፡ ይኸው፡ በዓይናችን እየተመለከትን እንገኛለን።

*ታዲያ!* እነዚህን፡ በብልሃታቸውና በገንዘባቸው፥ በኃይላቸውም ተመክተው የዘመቱብንንና የወረሩንን ተቃዋሚዎቻችንን፡ በምንም መጠንና ዓይነት፡ ልንወዳደራቸው ዓቅም የሌለን፡ እኛ፡ ደካሞቹ፡ እንዴት ነው፡ ልንቋቋማቸው የሚቻለን? ይህ፡ የዛሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የእግዚአብሔርን እውነት አምኖ ለመቀበል፡ ማንም ሳያስገድደው፡ ራሱ፡ “እምቢ!” ብሎ፡ አምላኩንና ቃል ኪዳኑን ካደ እንጂ፥ በአምላኩና በቃል ኪዳኑም ላይ ዐመፀ እንጂ፥ በአምልኮውም፡ አመነዘረ እንጂ፡ ተቃዋሚዎቹን፡ መቋቋም ብቻ ሳይኾን፡ እነርሱን የሚያሸንፍበት ብልሃት፥ ገንዘብና ኃይል እኮ፡ በራሱ፡ በየእጁ መዳፎች ውስጥ ጨብጦ ይዞት ይገኛል! እርሱም፡ የእግዚአብሔር የኾነው ብልሃት፥ ገንዘብና ኃይል ነው፤ ያም መለኮታዊ ሀብት፡ ተጠቃልሎ በውስጣችን የሚገኘውና ተዋሕዶን የምንኖርበት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ነው። ተቃዋሚዎቻችንን የምንገጥማቸው፡ በዚህ ሃይማኖታዊ የገድል መሣሪያችን ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ፡ እስከኖኅና እስከመልከጼዴቅ፥ በመጨረሻም፡ እስከመሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድረስ፥ ከዚያም ወዲህ፡ እስካኹኗ አፍታ ድረስ፡ ተቃዋሚዎቻችንን ኹሉ፡ ተቋቁመን፡ በቃል ኪዳናችን የሃይማኖት ኃይል፡ ድል የምናደርጋቸው፡ በዚሁ፡ “ገድል” በሚባለው፡ የራስን ሰውነትና ሕይወት፡ ለመሥዋዕትነት ማቅረብን በሚጠይቀው፡ ሰላማዊ ተጋድሎ መኾኑን፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ የምንገኝ ኹሉ እናውቀዋለን።

ለዚች ኢትዮጵያችንና ለዚህ ኢትዮጵያዊነታችን፡ ቀናተኞች ኾናችሁ የተነሣችሁ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹሉ፡ ይህ ጽኑ የተቃውሞ ፈተና፡ ከጥንት፡ የዘር ተቃዋሚዎቻችን ከኾኑት ኃይላት፡ በሥውርም ኾነ በግልጽ፥ በረቂቅም ኾነ በግዘፍ፥ በመንፈስም ኾነ በሥጋ፡ የሚጠብቃችሁ መኾኑን አውቃችሁ፡ ይህንኑ ፈተና፡ ለመቋቋም ብቻ ሳይኾን፡ ድል ለማድረግም፡ ቆርጣችሁ የተዘጋጃችሁ መኾን እንዳለባችሁ፡ እስካኹን፡ በተመለከታችሁትና በየራሳችሁ ላይ በደረሰባችሁ ሳትገነዘቡት እንዳልቀራችሁ፡ ተስፋ አደርጋለሁ።

ኢትዮጵያዊው መሪ አምላካችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ገድላችንን ኹሉ፡ ራሱ ፈጽሞት፡ እኛም፡ ይህን በመሰለው፡ የገድል ሰልፋችን ጊዜ ይረዳን ዘንድ፡ መመሪያ አድርገን እንድንጠቀምበት፡ “እነሆ፡ ኹሉን፡ አስቀድሜ ነገርኋችሁ!” ብሎ ባጠቃለለው የምክር ማስጠንቀቂያው፡ የተወልንን ቃሉን፡ በሚበቃ ታውቁታላችሁ፤ ቅዱሳን ሐዋርያቱ፡ ያን መመሪያ ተከትለው ከጻፉት መካከል፡ ጥቂቱን፡ እዚህ ላይ ልጠቅስልዎ እወድዳለሁ፡-

ይኸውም፡ “በቀረውስ፡ በእግዚአብሔርና በኃይሉ ችሎት፡ የበረታችሁ ኹኑ! የዲያብሎስን ተንኰል ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ ልበሱ! መጋደላችን፡ ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና! ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፥ ከዚህም፡ ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር፥ በሰማያዊም ሥፍራ ካለ፡ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ፡፡ ስለዚህ፡ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ኹሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ፡ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ኹሉ አንሡ!

“እንግዴህ፡ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት፡ እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ! በኹሉም ላይ ጨምራችሁ፡ የሚንበለበሉትን፡ የክፉውን ፍላጻዎች ኹሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን፡ የእምነትን ጋሻ አንሡ! የመዳንንም ራስ ቍር፥ የመንፈስንም ሠይፍ ያዙ! እርሱም፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ በጸሎትና በልመናም ኹሉ፡ ዘወትር፡ በመንፈስ ጸልዩ!”

ደግሞም፡ “በመጠን ኑሩ! ንቁም! ባላጋራችሁ ዲያብሎስ፡ የሚውጠውን ፈልጎ፡ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ፡ ያን መከራ፡ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ፡ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት!” የሚለው ነው፡፡ (ኤፌ. 6፥ 0-08፤ 1ጴጥ. 5፥ 8-9፡፡)

6ኛ፡ የመልስ ሓተታዬን ከመዝጋቴ በፊት፡ “ፍልስፍና” የሚለውን ቃል፡ በደብዳቤዎ ውስጥ ስለጠቃቀሱት፡ ቃሉ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን አኳያ፡ ምን ዓይነት ትርጓሜንና ስሜትን እንደሚሰጥ፡ እገልጽልዎ ዘንድ አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

“ፍልስፍና”፡ ሰብአውያን ምሁራንና ጠበብት፡ ስለእምነታቸውና ስለሕይወታቸው ምሥጢር፡ በሥጋዊው አእምሮአቸው ተራቅቀውና አስበው፡ በየግላቸው የሚያመነጩት የእውቀት፥ ወይም፡ የምርምር መላምት ስለኾነ፡ በሰዎች የትምህርት ብስለትና የአስተሳሰብ ጥልቀት፡ በየዘመናቱ የመለዋወጥ ጠንቅ፥ የኋላ ኋላም የመሻር ፍጻሜ ሳይደርስበት የሚቀር አይኾንም፤ የዚያ ፍልስፍና ጀማሪና መሥራች፡ ራሱ፡ “ፈላስፋ” ይባላል፤ ፍልስፍናውን የፈጠረው፡ ፍጡሩ ሰው በመኾኑ፡ “ፍልስፍና”፡ ሃይማኖት አለመኾኑ፥ ሊኾንም እንደማይችል፡ በዚህ ይታወቃል፡፡

የእኛ የኢትዮጵያውያን የሕይወት መመሪያ ግን፡ ፍልስፍና ሳይኾን፡ ሃይማኖት ነው፤ ይህንኑም ሃይማኖት፡ ጥንቱኑ፡ እግዚአብሔር፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ራሱ፡ በነፍሳችን አማካይነት ባስተማረን፥ በየልቦናችን ጽላት ላይ በጻፈልንና በየሕሊናችን መዝገብ ውስጥ ባሳደረልን፡ በቅዱሱ ኪዳን ተቀብለነው፥ አውቀነውና አምነንበት ኖረናል፤ በመደምደሚያውም፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም፡ እውን ኾኖልን፡ ለፍጹምነት በቅቶልናል፤ ስለዚህ፡ ሃይማኖታችን፡ ከፈጣሪ እንደተገኘ ጸጋና ኃይል እንጂ፡ ዓለማውያንና ሥጋውያን አዋቂዎች፡ ሰው እንደፈጠረው ፍልስፍና አድርገው የሚያቀርቡት መላምት፡ በአስተሰሰባችን ውስጥ እንዳይሠረፅ፥ በአድራጎታችንም ላይ እንዳይከሠት፡ በብርቱ ልንጠነቀቅበት እንደሚገባ ላሳስብ እወድዳለሁ፡፡

7ኛ፡ በመጨረሻ፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት፡ ያለን፡ አንድ አምላክና አባት፥ አንድ መምህርና ሊቅ፥ አንድ ካህንና ሊቀ ካህናት፥ አንድ መሪና አለቃ፥ አንድ ንጉሥና ንጉሠ ነገሥት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህ፡ ወደፊት፡ ስንጻጻፍ፡ ወይም፡ ስንነጋገር፡ ለእኔ የተሰጠኝ፥ እኔም የምቀበለው አጠራር፡ “አባቴ” የሚለውን ሳይኾን፡ “አገልጋዬ!” ወይም፡ “ካህኔ!” ወይም፡ “ቄሴ!” ቢበዛም፡ “ንቡረ እድ!” የሚለውን መኾኑን፡ እርስዎም፥ ተባባሪዎችዎም፡ እንድታውቁት ይኹን! ምናልባት፡ የተለመደው፡ ሌላ ኾኖ፡ ይህ አጠራር ግን፡ ያልተለመደ በመኾኑ፡ “ያስቸግራል!” ቢባል እንኳ፡ “እንደሌሎቹ ስሕተቶቻችን ኹሉ፡ ይህንም፡ እያረምንና እያስተካከልን፥ እያጠራንም መኼድ ይገባናል!” እላለሁ፡፡

ይህ አስተያየቴ፡ ከራሴ የመነጨ ሳይኾን፡ መሪ አምላካችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን መመሪያ የተከተለ መኾኑን፡ ትገነዘቡታላችሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ይኸውም፡ ለማስታወስ ያህል፡ ከመለኮታዊው መመሪያ፡ “እናንተ ግን፡ 'መምህር!' ተብላችሁ አትጠሩ! መምህራችሁ፡ አንድ ስለኾነ፤ እናንተም፡ ኹላችሁ፡ ወንድማማች ናችሁ፡፡ አባታችሁ፡ አንዱ፥ እርሱም፡ የሰማዩ ነውና፡ በምድር ላይ ማንንም፡ 'አባት' ብላችሁ አትጥሩ! ሊቃችሁ፡ አንድ፥ እርሱም፡ ክርስቶስ ነውና፡ 'ሊቃውንት!' ተብላችሁ አትጠሩ! ከእናንተ፡ የሚበልጠው፡ አገልጋያችሁ ይኾናል፡፡” የሚለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ (ማቴ. "3፥ 8-02፡፡)

እንግዴህ፡ እስከሚቀጥለው ግንኙነታችን ድረስ፡ አምላከ ኢትዮጵያ፡ በያለንበት ጠብቆ፡ በኪዳናዊው የኢትዮጵያዊነት ተግባራችን ተጠናክረን ለመቀጠልና ተገቢውን የሥራ ፍሬ ለማስገኘት፥ መዋዕለ ጾሙንም፡ በደህና አስፈጽሞ፡ ለብርሃነ ትንሣኤው፡ በሰላም ለመድረስ ያብቃን!

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ
የመእዘኢት. ተጠሪ አገልጋይ